# የኢህዴን-ብአዴን ታሪክ 1973 - 2008 መጽሀፍ ወይስ ያልተሟላ የመረጃ መጽሄት?

ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ 04-13-17

## መግቢያ

በዋነኛነት የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮተዊ ፓርቲ/ሠራዊት (ኢ.ህአፓ/ሠ) አካል ከነበረው የበለሳው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አባላት መካከል በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አልፈው፣ በትግል ጽናታቸው ተፈትነውና በአመለካከታቸው ጥራት ነጥረው በወጡ 39 አባላት የተመሰረተው የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢ.ህዴን) የአሁኑ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ታሪክ እንዲጻፍ አጥብቀው ይፈልጉ ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዱ ስለነበርሁ የኢ.ህዴን-ብአዴንን ታሪክ የያዘ መጽሀፍ በድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ መነሻነት በተወሰኑ የአመራር አባላት አማካኝነት ተዘጋጅቶ በማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ድጋፍ መታተሙን ስሰማ በእጅጉ ተደስቼ የነበረ ከመሆኑ የተነሳ መጽሀፉን አግኝቼ እስከማነብ ድረስ ጓጉቼ ነበር፡፡

ሆኖም ያ በእጅጉ የጓጓሁለት ‘መጽሀፍ’ በእጄ ገብቶ ማንበብ ስጀምር የጠበቅሁትን ያህል የተሟላ ሆኖ ስላላገኘሁት ከመበሳጨቴ የተነሳ የማንበብ ፍላጎቴን በእጅጉ ተፈታተነው፣ ይህም ሆኖ የታሪኩን ፍሰት በተሟላ መልኩ ለማወቅ ከነበረኝ ብርቱ ስሜት የተነሳ ንባቤን በትግልም ቢሆን ቀጥየ በማጠናቀቅ ይህችን አጭር መጣጥፍ አዘጋጅቼ እንካችሁ ለማለት በቃሁ፡፡ መጽሀፉ ላይ የተስተዋሉ ችግሮችን ዝርዝር በቀጣዮቹ አንቀጾች ለመመልከት የምንችል ሆኖ መጽሀፉ እውነት ነው የምላችሁ በስርአቱ ታስቦበት የተዘጋጀ ሳይሆን በይድረስ ይድረስ አይነት ስሜት ውስጥ ተሁኖ በግብር ይውጣ የተጻፈ ይልቁንም አዘጋጆቹ ሀላፊነት የጎደለው ስራ መሰራታቸው በግልጽ የተንጸባረቀበት መሆኑን ለመገንዘብ ግን ጊዜ አልወሰደብኝም፡፡

ይህም ሆኖ ከዚህ ቀደም ከነበረው የተበጣጠሰና ከወሬ ያላለፈ የታሪክ አያያዝና አዘጋገብ ሁኔታ በተለየ መልኩ የድርጅቱ ታሪክ ጠቅለል ባለ መልኩም ቢሆንም እንዲህ በአንድ ሰነድ ተዘጋጅቶና የድርጅቱን ማዕከላዊ ኮሚቴ ይሁንታ በማግኘት ታትሞ ለተደራሲያን መቅረቡ በራሱ መልካም ነገር ስለሆነ እንደ ጥሩ ጅምር ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከዛም አልፎ ይህን ሰነድ መነሻ በማድረግ በህይወት የሚገኙ መስራቾችና

በትግሉ ሒደት ውስጥ ክቡር መስወአትነት የከፈሉ ነባር ታጋዮች በተለይም ከምስረታው ጀምሮ በከፍተኛ አመራርነት እየተመረጡ ድርጅቱን በመምራት አሁን ላለበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ያደረጉ ታጋዮች ግለ-ታሪክ በራሳቸው ተነሳሽነት አሊያም በሞያተኛ ታግዞ ሊጻፍ የሚችልበትን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር ድርጅቱም ሆነ ይህን ሰነድ በማዘጋጀት ረገድ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ የአመራር አባላቱ ችሎታቸው የፈቀደውን ያህል ጥረት አርገው ይህንን ሰነድ አዘጋጅተው በማሳተም እንካችሁ በማለታቸው ሊመሰገኑ ይገባል እላለሁ፡፡

ይሁን እንጂ ይህንን ያልተሟላ ሰነድ በትዕግስተ አንብቤ እንደጨረስሁ የተፈጠረብኝን ቁጭት በዝምታ ከማልፈው ይልቅ በጽሁፍ መልክ በመግለጽ ለሌሎችም ሀሳቤን ማጋራት እንዳለብኝ በማመን የተመጠነ ምልከታየን በሚከተለው አኳኋን አቅርቤዋለሁና አንዳች ስሜት የሚሰጥ ከሆነ ተደሰቱበት ካልሆነም ቢያንስ በዚህ ጥቁምታ መነሻነት መጽሀፉን እንድታነበቡና በመጨረሻም የፈጠረባችሁን እውነተኛ ስሜት በጽሁፍ ብታካፍሉን ደስታየ ወደር አይኖረውም፡፡

## አቀራረብና ይዘት

በእኔ እምነት የድርጅቱ ታሪክ መጻፍ የነበረበት በሁለት ተከፍሎ ነው፣ በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ቅጽ የኢህዴን ታሪክ ላይ ብቻ በማተኮር ማለትም ከህዳር 11/1973 እስከ ጥር 17/1986 በነበሩት አመታት ውስጥ የነበረውን ሁኔታ በዋናናነት በትጥቅ ትግሉ ሒደት የገጠመውን ውጣ ውረድና የደርግ-ኢሰፓ መንግስት ከስልጣን ከተወገደ በኋላ በነበረው የሰላምና መረጋጋት ስራ የነበረውን አስተዋጽኦ በሚገባ በሚያሳይ መልኩ፣ ሁለተኛው ቅጽ ደግሞ ከጥር 17/1986 እስከ አሁን ድረስ ያለውን የመንግስት የእለት ከእለት እንቅስቃሴን እንዴት እንደመራ በሚያሳይ አኳኋን ተዘጋጅቶ ቢታተም ኖሮ ይበልጥ ስሜት ይሰጥ ነበር ብቻ ሳይሆን በይዘትም ጥልቀት ይኖረው እንደ ነበር ከወዲሁ ለመገመት አይከብድም፡፡

ይህም ባለመሆኑ ምክንያት ይህ ሰነድ የአንድን ትልቅ ድርጅት ያውም በከፊልም ቢሆን የኢትዮጵያን ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች አጠቃላይ የትግልና የድል ታሪክ የሚመለከት ጉዳይን እንደ ቀላል ነገር ጠቅለል ባለ መልኩ ለመዳሰስ የሞከረ ያልተሟላ የመረጃ መጽሄት ሊባል ካልሆነ በስተቀር ለታሪክ ተመራማሪዎችም ሆነ ለመጭው ትውልድ በማጣቀሻነት ሊያገለግል የሚችል ሰነድ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ከዛም አልፎ

የሀገራችን ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች በአጠቃላይና በቅርብ ጊዜ ውስጥ ድርጅቱን የተቀላቀሉ ግንባር ቀደም አባላቱ ቀርተው የድርርቱ መስራቾችን ጨምሮ በትግሉ የመጀመሪያ ወራትና አመታት በረሀ የገቡ የቁርጥ ቀን ታጋዮችን ትውስታ እንኳ በአግባቡ በያዘ መልኩ አደራጅቶ በመቅረብ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊያደርግ የሚችል ሰነድ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ቀጥለው በሚቀርቡት አንቀጾች በዝርዝር ለመዳሰስ እንደምሞክረው በቂ ዝግጅት ተደርጎበትና በድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤትም ሆነ በሰማዕታት ሀውልት ውስጥ የሚገኙት የድርጅቱ ሰነዶች እንኳ በአግባቡ ተፈትሸው በማጣቀሻነት እንዲያገለግሉ ያልተደረገበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ የመስራች አባላቱ ስምና ማንነት በተሟላ መልኩ ተገልጾ በፎቶ ግራፍም እንዲደገፍ ተደርጎ እንዲወጣ ያልተደረገበት ሁኔታ ሲታይ በእርግጥም የሰነድ ዝግጅቱ ያን ያህል ታስቦበት የተከናወነ ስራ ስለመሆኑ ያጠራጥራል፡፡

እንዲሁም ቀደም ሲል በእህአፓ የኋላ ኋላ ደግሞ ከድርጅቱ ምስረታ ዋዜማ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በአመራርነት ያገለገሉ ሰዎች ሀሳባቸውንና ትውስታቸውን በስርአቱ እንዲገልጹና ታሪኩ ሙሉ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የራሳቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያልተጋበዙበት ይልቁንም የመስራች አባላቱም ሆነ ከምስረታ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ወደ ድርጅቱ የተቀላቀሉ ታጋዮች ማንነትና በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበራቸው ጉልህ አስተዋጽኦ በዝርዝር ያልቀረበበት ሰነድ በመሆኑ ጉድለቱ እጅግ የበዛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ሌላው ቀርቶ ከምስረታው ጀምሮ በተካሄዱት የድርጅቱ ጉባኤዎች ሊቃነ መናብርት (ዋና ጸሀፊዎች) ሆነው በመመረጥ ያገለገሉ ሰዎች ስምና አጠቃላይ ስብዕና እንዲሁም የነበራቸው ወታደራዊና ፖለቲካዊ ሚና በትክክል ያልተገለጸበት ሰነድ ስለሆነ በእርግጥም ለማጣቀሻነት የሚበቃ የታሪክ መጽሀፍ ነው ለማለት የያስደፍር ሆኖ አልተገኘም፡፡ በድፍረት ይህን እንድል ያደረገኝ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርሁት የዚህ ድርጅት የትግል ታሪክ በከፊልም ቢሆን የሀገራችን ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች የትግልና የድል ታሪክ አካል ስለሆነ በደንብ ታስቦበትና ጊዜ ተሰጥቶት ጥልቀት ባለው ጥናትና ምርምር ላይ ተመስርቶ መጻፍ ሲገባው እንዲህ እንደ ዋዛ ተጠቅልሎ መቅረብ አልነበረበትም የሚል እምነት ስላለኝ ነው፡፡

ከዛም ባሻገር የኢህዴን-ብአዴን ታሪክ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጅ የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ከወሰነ በርካታ አመታትን እንዳስቆጠረ ቢነገርም ይህን ያልተሟላና ተፈላጊ

ማጣቀሻዎችን እንኳ በበቂ ሁኔታና በአግባቡ ሳይዳስስ የተዘጋጀን ሰነድ ጽፎ ለማሳተም አመታትን መውሰዱ ብቻ ሳይሆን መሰረታዊውን ነገር ሳያሟላ መቅረቡ በራሱ የሚያስገርም ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ የታሪክ ሰነድ ሊይዝ የሚገባውን መረጃ በተቻለ መጠን አሟልቶ እንዲቀርብ የተደረገው ጥረትም እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑን በቀላሉ መታዘብ ይቻላልና ነው፡፡ በተለይም ከድርጅቱ የትግል ታሪክ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ዋቢ መጽሀፍትና ጽሁፎች እንዲሁም የድርጅቱን ልዩ ልዩ ሰነዶች ጭምር በሚገባ ፈትሾ ድርጅቱ ያለፈባቸውን የትግል ሒደቶች በጥልቀት ሊያሳይ በሚችል መልኩ አለመዘጋጀቱ፣ እንዲሁም የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ጨምሮ የህወሀት ከፍተኛ አመራሮች ከድርጅቱ ምስረታ ዋዜማ ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ስለድርጅቱ ጥንካሬ እና መስራች አባላቱ የትግል ጽናት አስመልክተው የሰጧቸውን የምስክርነት ሀሳቦች በአግባቡ እንዲካተቱ አለመደረጉ በራሱ ሰነዱ በእርግጥም በይዘቱ የሳሳ እንዲሆን የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል ማለት ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ የተወሰኑ ምሳሌዎችን በማንሳት በአዘጋጆቹ ስንፍና ምክንየት ምን ያህል ጠቃሚ ሀሳቦች በሰነዱ ውስጥ ሳይካተቱ እንደቀሩ ለማሳየት ልሞክር፣ የኦህዴዱን መስራች አቶ አባዱላ ገመዳንና የደኢህዴኑን መስራች ዶ/ር ካሱ ኢላላን የምስክርነት ቃል ሚዛን ለመስጠት ብንቸገር እንኳ የህወሀቶቹን ነባር ታጋዮችና ከፍተኛ አመራሮች ምስክርነት ግን ወደ ጎን ልንተወው የሚገባ አልነበረምና እንደሚከተለው ጠቅለል ባለ መልኩ አቀርባቸዋለሁ፡፡ እስቲ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትርና ለረዥም ጊዜ ያህል የህወሀት-ኢህአዴግ ሊቀመንበር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ በ2003 ዓ.ም የኢህዴን/ብአዴን 30ኛ አመት በአል አከባበርን ምክንያት በማድረግ ከታሚሶል ኮሚኒኬሽን ጋዜጠኛ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ስለኢህዴን-ብአዴን አመሰራረትና በምስረታው ውቅት የነበረውን ሁኔታ ከገለጹበት የምስክርነት ቃል እንጀምር፡፡

እንደ አቶ መለስ ዘኔዊ ገለጻ ከሆነ ኢህዴን የተመሰረተበት ወቅት ደርግ አንጻራዊ የበላይነት የያዘበት ጊዜ ነበር፣ በዚህ ጊዜ አንድ አዲስ አጋር ድርጅት ተፈጠረ ማለት ለህወሀት ትልቅ ደስታንና ሞራልን የሚያስገኝ ነበር፡፡ ምክንያቱም በዚህ ወቅት ህወሀት ብቻውን የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት ማምጣት አይችልም ነበር፣ አዲሲቷን ኢትዮጵያ በጽኑ መሰረት ላይ ለመገንባት ደግሞ የኢህዴን መመስረት ትልቅ ፋይዳ ነበረው በሚል

መልኩ ከመግለጽ አልፈው ስለኢህዴን/ብአዴን መስራች ታጋዮች የትግል ጽናትና ከህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ታጋዮች እንዴት እንደሚለዩም ጭምር ሲገልጹ ደግሞ፡-

> አንድ ሰው ለአንድ መስመር ወይም ለአንድ ድርጅት ህይወቱን ከገበረ በኋላ ያ ድርጅት ጭራቅ ሆኖ ያንን ግለሰብ ሊውጥ ወይም የዛን ግለሰብ ተስፋ ሊያጨልም የሚችልበት ሁኔታ ሲፈጠር የሚኖረው ሁኔታ ከሞት ያለፈ ነው፣ ከሞትም የባሰ ነው፡፡ የታገሉለት ድርጅት ጭራቅ ሆኖ አላማቸውን ሲውጥ፣ ጉም ሆኖ ሲበን፣ ሲተን እና መሀል ሜዳ ተበትነው ሲቀሩ ያ በጣም አስከፊ ሁኔታ ነው፣ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ለመታገል መወሰን ለህወሀት አዲስ ነው፣ ከሽዎች ወደ አስሮች ተመልሶ በጽናት መቀጠል መቻል በእርግጥም ትልቅ የሆነ የአላማ ጽናትን ይጠይቃል፣ ኢህዴኖች ያን አስከፊ ሁኔታ ተሻግረው ነው የሄዱት፡፡ ህወሀቶች እንደዚህ አይነት መጥፎ ዕድል አልገጠመንም፡፡[1]

በማለት ነበር በወwቅቱ ኢህዴን/ብአዴን ውስጥ የነበረውን ፈታኝ ሁኔታ በሰላ አንደበታቸው ያረጋገጡትና የኢህዴን-ብአዴን መስራች ታጋዮችም ሆነ የተከታዮቻቸው የጽናት ደረጃ ምን ያህል ከብረት የጠነከረ እንደነበር የገለጹት፣ በአጠቃላይም አቶ መለስ ኢህዴን/ብአዴን የአማራ ክልል ህዝቦችን አታግሎ አስቸጋሪውን የደርግ ዘመን በድል አድራጊነት ማለፉ፣ ኋላም ላይ የሽግግሩን ወቅት ፈተና በጽናት መዝለቁና የ1993 ዓ.ምቱን የህወሀት ከፍተኛ አመራር ለሁለት መሰንጠቅ ተከትሎ በሀገሪቱ ላይ ሊደርስ ይችል የነበረውን ከፍተኛ የሆነ አደጋ በግንባር ቀደምነት ተንቀሳቅሶ በመቀልበስ ረገድ የተጫወተውን ወሳኝ ሚና ስመለከት ለወደፊቱም ብሩህ ተስፋን የፈነጠቀ ድርጅት ነው ብየ እንዳምን አድርጎኛል ሲሉ ነበር ሀሳባቸውን አጠናክረው የገለጹት፡፡

እንዲሁም የህወሀት ነባር ታጋይ የነበሩትና ረዘም ላለ ጊዜ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር በመሆን ያገለገሉት አቶ ገብሩ አስራት ሉኣላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ አሳትመው ገበያ ላይ ባዋሉት መጽሀፋቸው ውስጥ ስለ ኢህዴን-ብአዴን አስተዋጽኦ አንስተው ያሰፈረትን ሀሳብ ደግሞ ቀጥለን እንመልከት፡

> የአሁኑ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) የበረሓ ስሙ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) ነበር፡፡ ድርጅቱ ከኢህአፓ/ሠ ተገንጥለው በቀሩ ጥቂት አባላት የተመሰረተ ሲሆን በጸረ-ደርግ የትጥቅ ትግል የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ሆኖም ኢህዴን/ብአዴን ደርግን በመጣል ካደረገው ወታደራዊ አስተዋጽኦ ይልቅ የፖለቲካ

[1] ይኸንን ግልጽ የሆነ የምክርነት ቃላቸውን በጆሮው አደምጦ ለሚጋገጥ የሚፈልግ ሰው ካለ ዩ ቱብ ወስጥ ገብቶ መመልከት ይችላል፡፡

> አስተዋጾኦው ይልቃል፡፡ (ምክንያቱም) ተሀሀት ኢ.ህአሠን (በሀይል ቀጥቅጦ) ከትግራይ ካስወጣ በኋላና ኢህአፓም በይበልጥ በራሱ ውስጣዊ ችግሮች (ተተብትቦ) ከተበታተነ በኋላ ህወሀት መኻል አገር ውስጥ ከማን ጋራ ሆኖ ትግሉን እንደሚገፋ ቸግሮት ነበር፡፡[2]

ሲሉ ነበር የኢ.ህዴንን ወሳኝ የሆነ ፖለቲካዊ አስተዋጽኦ በማያሻማ ሁኔታ ያረጋገጡት፣ ከዚህም በተጨማሪ ኢ.ህዴን/ብአዴን 35ኛ አመት የልደት በአሉን ሲያከብር በአሁኑ ወቅት የመከላከያ ኢ.ታማዦር ሹም ሆነው የሚሰሩትና የህወሀት ነባር ታጋይ እንደሆኑ የሚታወቁት ጀነራል ሳሞራ የኑስ በሰጡት የምስክርነት ቃል በግልጽ ለማስገንዘብ እንደሞከሩት ራያ-ቆቦ አካባቢ በተካሄደው ውጊያ ላይ ከእኔ ጋር የኢ.ህዴን አካል የሆነችው ላብ አደር ክፍለ ጦር ተሳትፋ አባላቷ ግዳጃቸውን በሚገባ ተወጥዋል፡፡ በዚህ ወቅት ኡስማን አሸኔ[3] የተባለው የኢ.ህዴን ከፍተኛ አመራር ነበር ከእኔ ጋር አጠቃላይ ግንባሩን እንዲመራ ተመድቦ የነበረው ሲሉ ነበር የኢ.ህዴን ታጋዮች በትጥቅ ትግሉ ወቅት በመዋጋት ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ አዋጊነትም (በጀነራልነትም) ጭምር የነበራቸውን የነቃ ተሳትፎ ያረጋገጡት፡፡

እንዲሁም የትግሉን አስቸጋሪነት፣ ድል የማድረጉን ሁኔታ አይቀሬነት፣ የአባላቱን ጽናትና አይበገሬነት ፍንትው አድርገው በማሳየት ለአርሶ አደሩንም ሆነ ወጣቱን ለትግል በማነሳሳት ረገድ ጉልህ ሚና የነበራቸው የግጥም ስንኞች በሀሳብ ማጠናከሪያነት እንደ አግባብነታቸው በሰነዱ ውስጥ እንዲካተቱ አለመደረጋው በራሱ መሰረታዊ ስህተት ከመሆኑም በላይ ተደራሲያን የትግሉን አስከፊ ገጽታ ብቻ ሳይሆን የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ በአግባቡ መተንበያቸውን ጭምር እንዳንገነዘብ ያደረገ ይመስለኛል፡፡

ሌላው ቀርቶ አሁንም ድረስ ኢ.ህዴንን የህወሀት ፍጡርና መስራች አባላቱንም የህወሀት ተላላኪ ሆነው የሚያገለግሉ አማርኛ ተናጋሪ ህወሀቶች እንደሆኑ ተደርገው እንዲታዩ በርካታ ሰዎች በንግግርም ሆነ በመጽሀፍ መልክ እንዲሁም የመገናኛ ብዙሀኑን ጨምሮ በተለያዩ መጣጥፎች ጥረት ማድረጋቸው ግምት ውስጥ ገብቶ እነዚህን የተዛቡ አመለካከቶችን በሚያጋልጥና ስህተታቸውንም በአስተማማኝ ማስረጃ አስደግፎ በማረም የኢ.ትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይና የአማራ ክልል ህዝቦች ደግሞ በተለይ የመሪ

---

[2] ገብሩ አስራት (2007)፣ ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ፣ 4ኛ እትም፣ ገጽ 108፣

[3] ኡስማን አሸኔ ከኢህዴን መስራቾች ወስጥ አንዱ የነበረ ከመሆኑም በላይ በጊዜው የኢህዴን/ኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር በመሆን የሚታወቅ ሲሆን በ1982 ዓ.ም ወልዲያ ከተማ ከተያዘ በኋላ ህይወቱ አልፏል፡፡

ድርጅታቸውን ትክክለኛ ታሪክ በአግባቡ እንዲያውቁ ጥረት አለመደረጉ በእኔ እምነት ታሪካዊ ስህተት ነው፡፡

በተለይም በቅርቡ ታትመው ከወጡትና የበርካታ ኢትዮጵያዊያንን ቀልብ በእጅጉ ስበው ከነበሩት መጽሀፍት መካከል የአቶ ገብሩ አስራትና የኮሎኔል ፍስሀ ደስታ ስራዎች ስለ ኢህዴን አመሰራረትና ፖለቲካዊ ሚና ያሰፈሩትን ሀሳብ በጥልቀት ተመልክቶ በማስተባበልም ሆነ ሁኔታውን በማብራራት በዚህ ሰነድ ውስጥ አንድም ነገር አለመባሉ እውነት ነው የምላችሁ በጣም አሳዝኖኛል፡፡ ከዚህም ባሻገር የመስራች አባላቱን ዝርዝር የሚያሳየውን ሰንጠረዥ ጨምሮ በተደጋጋሚ በዋቢነት የተጠቀሱ አመራሮችና መስራች አባላት ስም ከእነ አባታቸው ብሎም የትግል ስማቸው በተገቢው መጠቀስ ሲገባው በነጠላ ስም ብቻ መቀመጡ አንድም ስመ ሞክሼ ሰው ቢኖር አንዱን ከሌላኛው ለመለየት የማያስችል እንዲሆን አድርጓል፣ ሁለትም በትጥቅ ትግሉ ወቅት ለየት ባለ ስያሜ የሚታወቁ የድርጅቱ አመራሮችን በግርጌ ማስታወሻ ወይም በቅንፍ ውስጥ አስቀምጦ ተደራሲያን በአጠቃላይና የአህዴን ታጋዮችና የነባር ነጻ መሬት ነዋሪዎች በተለይ የተሻለ ትውስታ እንዲኖራቸው ማድረግ አለመቻሉ እንደ አንድ ትልቅ ክፍተት ተደርጎ መታየት ያለበት ይመስለኛል፡፡ ይህም በትግሉ ሒደት ላይ የነበሩ ክስተቶችና እነዚህ ክስተቶች በድርጅቱ እንቅስቃሴ ላይ ይፈጥሩት የነበረው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሁኔታ በአግባቡ ተዘግቦ እንዳይገኝ ያደርጋል፣ በዚህ ረገድ

አዲሱ ለገሰ (አዲሱ ኦቦ)፣

ተፈራ ዋልዋ፣ (        )

ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ)፣

ተሾመ እሸቱ (ሀባር)፣

ዮሴፍ ረታ (ገይድ)፣

ሲሳይ አሰፋ (ፂሞ)፣

አባተ መኮንን (ጎንቢሶ)፣

ይርጋ አበበ (ሀው ጃኖ)፣

ከበደ ጫኔ (ጣሳ) እና

ካሳ ተ/ብርሀን (ሸሪፎ)

በግንባር ቀደምነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ይመስለኛል፣ በአጠቃላይ በዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ አጽንኦት ሰጥቼ ለመግለጽ እንደሞከርሁት የኢህአፓ ዋነኛ ክፍል ከነበረው የበለሳው ዴመክራሲያዊ የእርማት ንቅናቄን መነሻ በማድረግ የተመሰረተ የፖለቲካ ድርጅት እንደ መሆኑ መጠን የክፍሉ ታደሰን ያ ትውልድ መጽሀፍትንና ሌሎች በኢህአፓ ታሪክ ዙሪያ የተጻፉ ልዩ ልዩ ሰነዶችን በዋቢነት ሳያካትት የወጣ ጽሁፍ መሆኑና ይህ ስህተት የተፈጸመው ደግሞ አብዛኞዎቹ መስራች አባላት በህይወት እያሉ መሆኑ ሲታሰብ እውነት ነው የምላችሁ ይበልጥ ያስቆጫል፡፡ ከዛም አልፎ ከምስረታው በፊት ለበርካታ ወራት (ከአምስት ወር ላላነሰ ጊዜ) በእርማትና በመስመር ማጥራት እንቅስቃሴ ላሳለፈና ይህንንም የእርማትና የመስመር ማጥራት ስራ በበርካታ ጥናታዊ ጽሁፎች አስደግፎ ለመስራች አባላቱ ለማብራራት ጥረት ላደረገ ንቅናቄ በርካታ ቃለ ጉባኤዎችና የማብራሪያ ጽሁፎች ተጠቅሰው ሰነዱ በእጅጉ የሚዳብርበት ሁኔታ አለመፈጠሩ እነዚህ ሰዎች ከታሪክ አጻጻፍ ስልት ይህን ያህል የራቁ ናቸው እንዴ ያሰኛል፡፡ እንዲሁም በንቅናቄው ውስጥ ከፍተኛ ሚና የነበራቸው አመራሮችና ግንባር ቀደም ተዋናዮች የግል ማስታወሻ በበቂ ሁኔታ በማጣቀሻነት እንዲያገለግል አለመደረጉ (የአንድ ሰው የግል ማስታወሻ ብቻ አንድ ጊዜ ከመጠቀሱ በስተቀር)፣ የችግሩን ደረጃ ያገዝፈዋል፡፡

ባለፉት 36 አመታት ውስጥ ከአስር በላይ ጉባኤዎችንና ለቁጥር የሚያታክቱ የማዕካላዊ ኮሚቴ ስብሰባዎችን ላካሄደ የፖለቲካ ድርጅት ቃለ ጉባኤዎች ውስጥ የአንድ ድርጅታዊ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ብቻ መጠቀሱ ሲታይ አንድም በድርጅቱ ውስጥ የሰነድ አያያዝ ችግር መኖሩን ሊያመለክት ይችላል፣ ሁለትም ይህ ታሪከዊ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲታተም ይሁንታ የሰጠው አመራርም ሆነ በዝግጁ ላይ በቀጥታ የተሳተፉት ሰዎች ለድርጅቱ ሰነዶች ያን ያህል ዋጋ አለመስጠታቸውን በግልጽ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ከ37 በላይ ቁጥር የነበራቸው መስራቾችን ይዞ የተደራጀና በሒደቱም ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ክረክር እያካሄደ አልፎ አልፎም ቢሆን የልዩነት ሀሳቦችን እያስተናገደ የመጣን ድርጅት ታሪክ ሲጻፍ የአንድ አባል ማስታወሻ ብቻ ተጠቅሶ መታለፉ እንዲሁም የብርጋዴር ጀነራል አከለ አሳየ መጽሀፍት እንኳ በዋቢነት

አለመጠቀሳቸው ጸሀፊዎቹ የግላቸውን ትውስታ ብቻ መሰረት አድርገው ያዘጋጁትና ሌሎች መስራቾችም ሆኑ ነባር ታጋዮች ሀሳባቸውን እንዲያካፍሉም ሆነ የግል ማስታዎሻዎቻቸው በማጣቀሻነት እንዲያገለግሉ ያልተደረገበት ሰነድ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የሚገርመው ነገር ሰነዱን በሀላፊነት እንዲያዘጋጁ የተመረጡት አመራር አባላት የድርጅቱ መስራቾችና ለረዥም ጊዜ ያህል የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ሆነው ያገለገሉ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ይህን ሰነድ ከማዘጋቸታቸው ቀደም ብለው የየግላቸውን አቋምና ትውስታ ሊያንጸባርቁ የሚችሉ መጽሀፍትን አዘጋጅተው በማሳተም  የተሻለ ልምድ ያላቸው ሆነው ሳለ በዚህ ሰነድ ዝግጅት ላይ የዚህ አይነት የግብር ውጣ ስራ በመስራት ግዴለሽነት የተንጸባረቀበት አቀራረብ መከተላቸው ነው፡፡ የ36 አመት የትግልና የድል ታሪክ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ቀርቶ የ36 አመት ዕድሜ ባለቤት የሆነ ጎልማሳ ግለ ታሪክ ሲጻፍ እንኳ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን ተደራጅቶና የበርካታ ሰዎችን አስተያየት ታሳቢ አድርጎ ነው ለህትመት የሚበቃው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት መሰረታዊ ጉዳይ ኢህዴን-ብአዴን ባሳለፋቸው አስር የትጥቅ ትግል አመታት ውስጥ ምን ያህል ታጋዮች ተሰው የሚለው ሁኔታ ነው፣ በዚህ ረገድ ለምሳሌ ህወሀት ከስልሳ ሽህ ያላነሱ ታጋዮችን ገብሬ መጥቻለሁ በማለት በተደጋጋሚ ሪፖርት ሲያደርግ ይደመጣል፣ ኢህዴንስ? እኔ እስከማውቀው ድረስ አሁንም ጭምር ከኢህዴን ጋር ታግለው የተሰው ታጋዮች ቁጥር በግልጽ ሲነገርም ሆነ ሪፖርት ሲደረግ አልሰማሁም፣ ለምን?

ሌላው በዚህ ሰነድ ውስጥ ሊነሳ የሚገባው አንድ እጅግ ጠቃሚ የሖነ ጉዳይ ሀሳብን በነጻነት የማራመድ ሁኔታን አስመልክቶ በሰነዱ ውስጥ የሰፈረው ሀሳብ በድርጅቱ ውስጥ አልፎ አልፎም ቢሆን ይከሰት የነበረውን ጸረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ የሚሸፋፍን ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ይህም ማለት ኢህዴን-ብአዴን ከምስረታው ጀምሮ የሀሳብ ፍጭትንና ልየነቶችን ከሞላ ጎደል ተግባራዊ ለማድረግ አየሞከረ የመጣ እንደሆነ ቢታወቅም በሰነዱ ውስጥ በተገለጸው መልኩ ሙሉ ለሙሉ ከጉድለት የጸዳ ነበር ለማለት ግን ስለድርጅቱ ካለኝ መረጃና አንጻራዊ እውቀት አንጻር ስመዝነው ያን ያህል ዴሞክራሲያዊ ነበር ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ ነበር ብሎ መደምደም የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ይህንንም ሀሳቤን በአስተማማኝ ማስረጃ አጠናክሬ ለመግለጽ ያህል በሁለት ምሳሌዎች አስደግፌ በሚከተለው መልኩ ለማቅረብ እሞክራለሁ፡

**ምሳሌ አንድ፡** በ1981 ዓ.ም በኢ.ህዴን ውስጥ የነበረው የማርክሲስት ሌኒኒስት ሀይል ራሱን ችሎ ይደራጅና የመሪነት ሚናውን ይወጣ የሚል ሀሳብ የፖለቲካ አመራሩ አካል ከነበሩ ሰዎች መካከል ተነስቶ ውይይት በተደረገበት ወቅት የተወሰኑ የድርጅቱ መስራች አባላት የተለየ አመለካከት በመያዛቸው ምክንያት የወረደባቸው የሂስ መዓትና ይህን ተከትሎ ከድርጅቱ ይባረሩ የሚል ሀሳብ እስከማቅረብ ተደርሶ የነበረ መሆኑ ሲታይ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ የትግል ስልት በግልጽ ተንጸባርቆ እንደነበረ ያመለክታል፡፡

ይባስ ብሎም እነዚህ ታጋዮች ለዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ህይወታቸውን ለመስጠት ዝግጁ ሆነውና ከምስረታው ጀምሮ ያን ሁሉ መከራና ስቃይ በጸጋ ተቀብለው እያስተናገዱ መጥተው ድርጅቱ አንጻራዊ የሆነ ጥንካሬ ማግኘት በተጀመረበት ወቅት ከመባረር በመለስ ነገር ግን ከሀላፊነታቸው እንዲነሱ ተደርጎ በተራ አባልነት እንዲቀጥሉ የተወሰነበትና ከአመራሩም ሆነ ከግንባር ቀደም አባላቱ ለተወሰነ ጊዜ ያህልም ቢሆን ተገልለው እንዲቆዩ የሚያደርግ ሁኔታ ተፈጥሮ የነበረበት የትግል አግባብ የሰነዱ አዘጋጆች የደሰኮሩለትን ያህል የድርጅቱ አመራር ፍጹም ዴሞክራሲያዊ ነበር ለማለት የሚያስችል እንዳልነበር በተለይም ለነባሮቹ የኢ.ህዴን/ብአዴን ታጋዮች ብዙም የተሰወረ ጉዳይ አይደለምና በልክ ቢባልለት ጥሩ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ታጋይ ዮሴፍ ረታ (ገይድ) እና ታጋይ ተሰማ ገ/ህይወት ላይ የተወሰደው የቅጣት እርምጃና የማግለል ተግባር ግለሰቦቹ አይበገሬና የመርህ ሰዎች ስለነበሩ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ሳያሸነፋቸው በጽናት ተወጡት እንጂ በጊዜው በሞራላቸውና በመታገል ስሜታቸው ላይ ፈጥሮት የነበረውን አሉታዊ ጫና በቅርብ ለምናውቃቸው ሰዎች ግልጽ ነበር፡፡

ይህንንም ሀቅ በ1983 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ሀገረሰላም ውስጥ በተካሄደው የኢ.ህአዴግ መስራች ጉባኤ ላይ የሚሳተፉ አባላትን ለመምረጥና በጉባኤው አጀንዳዎች ላይም ለመምከር አላማጣ ከተማ ውስጥ ተዘጋጅቶ በነበረው የካድሬዎች መድረክ ላይ ታጋይ ዮሴፍ ረታ (ገይድ) በተፈጸመበት የማግለል ድርጊት ስሜቱ በእጅጉ ተጎድቶ እንደነበረ በግልጽ ማንጸባረቁ ይታወሳል፡፡ የሚገርመው ነገር እነዚህ የመርህ ሰዎችና ንጹህ ታጋዮች በወቅቱ በድፍረት ያራመዱት ፖለቲካዊ አቋምና አመለካከት የኋላ ኋላ ትክክል እንደነበር በተግባር ተረጋግጦ ድርጅቱም ውሾን ያነሳ ውሾ በሚል አይነት አቀራረብ የኮመኒስት ፓርቲው አባላትም በስርአቱ እንኳ እንዲያውቁትና ሀሰባቸውንም እንዲሰጡበት ሳይደረግ መቅረቱ ይታወቃል፡፡

በሌላ አባባል የኮሚኒስት ፓርቲው ህልውና ማብቃቱ በግልጽ ተነግሯቸው የቀብር ስነስርአቱን እንኳ በአግባቡ እንዲፈጽሙ ሳይደረግ በአመራሩ ውሳኔ ብቻ በዝምታ ታልፎ ወደ ቀደመ ይዞታው የተመለሰበት ሁኔታ እንደነበር እየታወቀ እነዚህ ታጋዮች ባራመዱት ትክክለኛ ሀሳብ ሳቢያ በአመራሩና በየደረጃው በነበሩት ግንባር ቀደም ካድሬዎች ለተፈጸመባቸው ግፍና በደል ይቅርታ አለመጠየቃቸው ብሎም በዚህ ሰነድ እንኳ እውቅና ለመስጠት አለመፈለጉ ሲታሰብ አሁንም የኢህዴን-ብአዴን አመራር ከስህተቱ ለመማርና እውነትን ፊት ለፊት ለመጋፈጥ ዝግጁ አለመሆኑን ሊያሳይ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊባል ይችላል? ከዛም አልፎ ስለኮምኒስት ፓርቲው ምስረታ ሒደት የተወሰነ የተባለውን ያህል እንዲፈርስ የተደረገበት አካሄድ ኢ-ዴሞክራሲያዊ እንደነበር መግለጽም ተገቢ ነበር ብየ አምናለሁ፡፡

**ምሳሌ ሁለት** በ1983 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የወልዲያ ሪጅን አመራር የነበረው ይርጋ አበበ (ሀው ጃኖ) በህወሀትና በኢህዴን መካከል ያለው ግንኙነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አይደለም፣ ህወሀት የበላይ ኢህዴን ደግሞ የበታች ሆነው የሚታዩበት ሁኔታ አለ፣ የዚህ አይነቱ ሁኔታ ደግሞ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥም የህወሀት አባላት የበላይነት ስሜት በግልጽ እየተንጸባረቀ መሆኑን አብረውት በሪጅን ኮሚቴ አባልነት ይሰሩ ከነበሩ የህወሀት ታጋዮች በተግባር የተመለከተውን በምሳሌ አስደግፎ ለድርጅቱ ከፍተኛ አመራር በማቅረብ ይኸ ሁኔታ በጊዜ ሊታረም ይገባዋል የሚል አቋም ማራመዱና ይህንን እምነቱንም በጽሁፍ ጭምር አዘጋጅቶ አባላት እንዲወያዩበት መጠየቁ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ይህንን አቋሙን ለማስቀየር በአቶ መለስ ዜናዊና ታምራት ላይኔ ጭምር ተሞክሮ የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ በህወሀት ሰዎች ግፊትም ይሁን የኢህዴን አመራር በራሱ ተነሳሽነት እስካሁንም ድረስ እርግጠኛ ባልሆንሁበት ሁኔታ ይርጋ አበበ (ሀው ጃኖ) የያዘው ፖለቲካዊ አቋም እጅግ አደገኛና ከእህት ድርጅት ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያሻክር ነው በሚል ሽፋን ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት የታገደበትና አስተሳሰቡም ወደ አባላት እንዳይወርድ የታፈነበት አጋጣሚ የነበረ ከመሆኑም በላይ የኋላ ኋላ ለህይወቱ መጥፋት ምክንያት የሆነውን የይታሰር እርምጃ የወሰደበት አጋጣሚ መኖሩ ሲታይ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ምን ያህል ችግሮች ይስተዋሉበት እንደ ነበረ በግልጽ ያመለክታል፡፡

ይህም ሆኖ በርካቶች እውቅና ለመስጠት ይቸገሩ እንጂ ባለፉት 40 አመታት በሀገራችን በተካሄዱ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የኢ.ህዴን-ብአዴን ሚና እጅግ ግዙፍ የነበረ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ታሪኩ በትክክል ተጽፏል ማለት ባይቻልም በመነሻነት ሊታይ የሚችል ሰነድ መኖሩ በራሱ መልካም ስለሆነ ሰነዱ ሊነበብና በሒደትም ሊዳብር ይገባል እላለሁ፡፡ በሌላ አገላለጽ ባዶ ምንም ነገር መኖሩ ይሻላል በሚለው አባባል አጥብቄ ስለማምን ይህንን ሰነድ እንደ አንድ መነሻ በመውሰድ የጎደለውን ለማሟላት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የተሻለ ስራ ሊሰራ ይችላል የሚል እምነት ስላለኝ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆኑ በቀጥታም ይሁን በተዛዋሪ ይመለከተናል የሚሉ ወገኖች ሁሉ ሰነዱን አንብበው ስለ ድርጅቱ የትግል ሒደት እንዲያውቁና ሀሳባቸውንም እንዲገልጹ እጋብዛለሁ፡፡